የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀራጥ ልጆቿ ለዘመናት አስከብራ የቆየችውን ሃይማኖት፣ ሥርዓት፣ ቀኖናና ትውፊት ለማስከበር ለአያሌ ዓመታት ሲፋለሙ የቆዩ አባቶች ካህናት፣ ወንድሞች ዲያቆናት፣ እናቶችና አባቶች ወንድሞችና እኅቶች እንዲሁም ሕፃናት ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነፃነት አስፈላጊ እንደሆነ አውቀው ወደ እውነተኛዋና ቀጥተኛዋ የሃይማኖት መንገድ ለመጓዝ በቁርጠኝነት ተነስተው ሰው ሊኖር የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በመረዳት ካህናት ደሞዝና ቤታቸውን ምእመናን ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ያፈሰሱበትን ቦታ ትተው በፈተና መካከል መናፍቃንንና ፈታኝ ዲያብሎስን ዘወትር ድል እየነሣች ከምትኖር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ



## እሑድ መጋቢት ፳፰/፳፻፮ ዓ.ም.

ለመኖር ወደ ቀደመው ነገር እንመለስ በማለት የተጓደለው ሥርዓት ተሟልቶና የፈረሰው ቀኖና ተገንብቶ በቤተ ክርስቲያኗ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ገብቶ አብሮ ለመሥራት የተወሰደው ርምጃ ጊዜው ለሚጠይቀውና ለጠየቀው ጉዳይ ታላቅ ሰማዕትነት ለከፈሉ ካህናትና ዲያቆናት፣ እናቶችና አባቶች፣ ወንድሞችና እኅቶች እንዲሁም ሕፃናት ሊቃነ ጳጳሳትና ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ትምህርት ቤት ማስታወሻ እንዲሆን የጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ትምህርት ቤት ፲፰ኛ ዓመታዊ በዓሉን ባከበረበት ወቅት በአውደ ምሕረቱ ላይ የተነበበ።

# ጊዜው የጠየቀው ሰማዕትነት።

እግዚአብሔር ያልብሰን ክብር እን ደ ሙሴ፣
ዝንቱ ኵሉ ኮነ አሜን በሥላሴ።
ሁሉን ያዘጋጀ እግዚአብሔር ነውና፣
ለዚች ቀን ደረስን በቃን ለምስጋና።



እየመራ አወጣን ታደገን ሚካኤል፣
የድንግል ልጅ ጌታ ብትፈቅድ አማኑኤል።
ምስጋና ብቻ ነው በሰማይ በምድር፣
ለአምላክ ልዩ ሥራ ለእግዚአብሔር ተአምር።
መላእክት በሰማይ የሰው ልጅ በምድር፣
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር።




ካህናት ቀደሙ እኛም ተከተልን፣
ክብር ውዳሴ ለአንተ ንሴብሖ እያልን።
ለሁሉ አባት ናችሁ የቤታችን ኩራት፣
ሐሴት አድርገናል በእናንተ ካህናት።

ሁሉ በአንተ ሆነ አምላክ መድኃኔዓለም፣
ስምህ አሸነፈው ጨለማውን ዓለም።
የእምነት ዱካችሁን ተከትለን መጣን፣
እናንተን የመራው እግዚአብሔር ረዳን።
ማነው እርፉን ይዞ ወደ ኋላ የሚለው፣
እግዚአብሔር ከፍቶታል የሚዘጋው ማነው?
በጎቹን ጠብቁ እረኞቹ ናችሁ፣
አደራዬን ስሙ የሚል ቃል ደርሷችሁ፣
ይኽን ኃላፊነት ገንዘብ አድርጋችሁ፣
ሕዝበ ምእመናኑን በጸሎት ባርካችሁ፣
ሕፃናቱን ደግሞ ጥምቀት አጥምቃችሁ፣
ያዘነ አጽናንታችሁ የሞተ ፈትታችሁ፣
ምክር ለፈለገው ጎኑ ተገኝታችሁ፣
ለትዳር ቢመጣ ተክሊል አድርሳችሁ፣
ሕዝቡ በወንጌል ቃል ታንጾ ተምሮ፣
እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ልቦናው ተሰብሮ፣
መልካም አርጋችኋል የእግዚአብሔር ቡሩካን፣
መሥዋዕታችሁ ሰምሯል የቀረበው ዕጣን።



እሑድ መጋቢት ፳፰/፳፻፲፩ ዓ.ም.

ስንቱ ሸክም ኖሮት ሲቀርብ እናንተጋ፣
ተፈውሶ ሄዷል በዝቶላችሁ ፀጋ።
በወንጌል ቃላችሁ ይኽው በዝቷል ምሕረት፣
የሕይወት ቃል ሰሙ ከሰማይ ከገነት።



እሑድ ሚያዝያ ፲፪/፳፻፲፩ ዓ.ም.

አባት ይኽንን ሕዝብ ካህን አታሳጣው፣
እምነቱን የሚያሳይ መንገድ የሚመራው።
ዕውቀት ያፈሰሰው ገንዘብና ጉልበት፣
ያገለገለህ ሕዝብ መንፈስ ይረፍበት።
ዝንቱ ኵሉ ኮነ በሥላሴ ፍቃድ፣
ዲያብሎስ አፈረ መሠረቱ ሲናድ።
ታሪክ ተቀይሮ ትናንትን ያለፍነው፣
መድኃኔዓለም ፈቅደህ ከፊት መርተኸን ነው።
እንዲህ ሳይደከም ውጤት ሳይለካ፣
ከወዴት ይገኛል የታለ ፋሲካ?
አንተ አባት ተደሰት አንቺ እናት እልል በይ፣
የከበርንበት ቀን ይኼው አይደለም ወይ።

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ሁሉን ፈጽምልን፣
መልአከ አርያምን በዕድሜ ጠብቅልን።



# መልአከ - አርያም ቀሞስ
# አባ ኃይለ - ሚካኤል

ትዕግሥት አስተማረን አፉ ሳይናገር፣
ዝምታው መልስ ሆነ ሰይጣን እስኪሰበር።
አመስግኖ የሚያድር ታላቁን የእምነት ሰው፣
መልአከ አርያምን ለሕዝብህ መርጠኸው፣
እንዲያገለግልህ ቀድመህ የወሰንከው፣
የቀባኸው ካህን ይኸው ከእኛ ጋር ነው።
እያመሰገነ በወንጌል ቃል ታምኖ፣
እኛን ይባርካል ቤተ መቅደስ ሆኖ።
የሥላሴ አገልጋይ የቅድስት ማርያም፣
የዚህ ሕዝብ አባት ነህ መልአከ አርያም

ታላቅ ትሕትናህ የእምነትህ ትጋት፣
ዝምታህ ሰው ገዛ የትዕግሥትህ ብዛት።
ሃይማኖቴን ያለ አባት ያስፈለገው፣
ተከትሎህ መጥቷል በመስቀልህ ባርከው።

ባርኮት አፍስስበት ይበል ክብር አየሁ፣
የአንተ አገልጋይ ባርያ መምህር ስንታየሁ።
እንደበቱን ባርከው ከሳሻችን ይፈር፣
ወንጌል አመስጥሮ በሙላት ይናገር።



# መምህር ቀሲስ ስንታየሁ ደምስ

የቃልህን ምሥጢር አኑር በአንደበቱ፣
ለብዙዎች ተስፋ እንዲሆን ስብከቱ።
ወንጌልን ሲናገር ምሥጢር እያስማማ፣
ኃይል ይወጣል ከአፉ ስለሆንከው ግርማ።
ባለው ላይ ክርስቶስ ደጋግመህ አብዛለት፣
ልጅህ የፀና ነው በኦርቶዶክስ እምነት።
እንድናድግ አድርጎናል በሃይማኖት ፍኖት፣
በረከቱ አድሮበት የአባ ተክለ-ሃይማኖት።

አሁንም አሁንም ከፀጋህ አብዛለት፣
ለብዙዎች ሞገስ እንዲሆን በስብከት።

መምህር አሐዱን ባርከው በአገልግሎት፣
ደጋግመን እንድናይ የወንጌልን ፍኖት።
የሚናገረው ቃል መጥቶ ይዋሐደን፣
ፀጋህን አብዛለት በወደድከው መጠን።



# መምህር ቀሲስ አሐዱ አሰፋ።

ብዙዎች ምእመናን ከቃሉ ተምረው፣
በኦርቶዶክስ እምነት እንዲኖሩ ፀንተው፣
ገንዘብ አድርገለት ስብከቱ ሰው ይግዛ፣
በአፉ ውስጥ ይጣፍጥ የቃልህ መዓዛ።
ጉባኤ ዘርግቶ ዘወትር ሐሙስ ዕለት፣
ሲሰብክ ሲያስተምር ይኸው ዓሥር ዓመት።
ብዙዎች ተምረው ተረድተው አውቀዋል፣
ይቺ ናት ኦርቶዶክስ ብለው መስክረዋል።
ዛሬም እንዲቀጥል የዓሥሩ ዓመት ፍኖት፣
ክርስትናን ያጽናው ሰብኮልን ሃይማኖት።

ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ የክህነት ዕውቀቱን፣
አባት ጨምርለት ማስተዋል ጥበቡን።



**ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ።**

የሚባርክ አባት ይብዛልን በቤቱ፣
ዕውቀት ማስተዋልን ወርሶታል ከአባቱ።
ቅዳሴና ዜማ ያምራል ከአንደበቱ፣
የካህን ልጅ ካህን ሙሉ ነው ዕውቀቱ።
በፀጋ ላይ ፀጋ በክብር ላይ ክብር፣
ይሰጥ ይታደለው ሳለ በዚህ ምድር።
አባት ሆይ አብዛለት እውቀትና ጥበብ፣
ክህነቱን ዝንተ-ዓለም አድርግለት ገንዘብ።
በሙላት አናግረው የወንጌልህን ቃል፣
በኃይልህ እግዚአብሔር ሰው ይድንበታል።

ቀሲስ መጽናኛዬ ለቤትህ ሲተጋ፣
አባት አፍስስበት በፀጋ ላይ ፀጋ።
ለቤትህ ሥርዓት እጅግ የሚቀና፣
ሕይወቱን አጥሮታል በስምህ ምስጋና።
ቃልን በማስተማር በመዝሙር በጸሎት፣
ፍሬ ይመግበን በፍጹም ሃይማኖት።



**ቀሲስ መጽናኛዬ**



**ቀሲስ ጸሊማዮሁ**

ቀሲስ ዓለማየሁ ሲቆም በዐውደ ምሕረት፤
አባት እንደበቱን ያሰለጠንክለት፤
መምህረ ወንጌል ስብከቱ ምግብ ነው፤
ከልዑል እግዚአብሔር ከላይ የተሰጠው።
ዛሬም ቃል እንማር ከአንደበቱ እንስማ፤
በወንጌል ትለምልም የያዝናት ከተማ።



## ቀሲስ ቸርነት

ትሕትናው ለበዛ እጅህ ላረፈበት፤
ለቤትህ አገልጋይ ለቀሲስ ቸርነት፤
በእምነት አጽንተኸው ዘይቱን ቀብተህ፤
ለቤትህ ጠራኸው ማስተዋልን ሰጥተህ።
ዛሬም እንደ ትናንት አንተ እንደፈቀድከው፤
ለአንተ የተለየውን ሕዝብህን ይባርከው።
አንተ የመረጥከው የቤትህ አገልጋይ፤
ክብር መሥዋዕቱ ይደርሳል ከሰማይ።

ትንሽ ታናሽ ሲባል በሰዎች አንደበት፤
በፊትህ ታላቅ ነው ዲያቆን ኤፍሬም ማለት።
ገና አታውቅም ሲሉት ሞኞቹ በአፋቸው፤
እሱ ራእይ አይቷል ማን በነገራቸው።



## ዲያቆን ኤፍሬም

ለሃይማኖት ዕውቀት ቤተሰቡን ትቶ፤
ገዳም ሄዶ ኖረል ትሕትና አሳይቶ።
የአባቶቹ መንገድ በሩቅ እየታየው፤
"ይብቃን" ይል ነበረ መለያየት እንተው።
ከነስምህ ኤፍሬም ባርኮት የደረሰህ፤
እግዚአብሔር ታናሹን ታላቅ አደረገህ።
እንደ መጽሐፉ ጥንት እንደተጻፈው፤
ያዕቆብ ቀኝ እጁን ነው ኤፍሬም ላይ የጫነው
ከአባቶችህ ጋራ ያቁምህ በጽናት፤
አምላኬን ብለኻል ገና ሳለህ ወጣት።

ዲያቆን ዮሴፍ ፍቅሬ ገረመው ትንሣኤ፤
ምሳሌዎች ናችሁ በዚህ በጉባኤ።
ዲያቆን ዳዊት ሄኖክ ኤርምያስ በለጠ፤
ከሁሉም ይበልጣል ለእናንት የተሰጠ።
እናንተ ዲያቆናት ከፍ ይበል ክብራችሁ፤
ከዚህ ዓለም ጥቅም አምላክን አላችሁ።
ከአባቶቻችሁ ጋር ከአበው ካህናቱ፤
ድል አድርጋችኋል በእውነት ዲያቆናቱ።



# ዲያቆናት በአገልግሎት

ለብዙዎች ዛሬ ምሳሌ ሆናችሁ፣
በአምላክ ፊት ይባረክ አገልግሎታችሁ።
አሁን መልካም መንገድ ረግጧል እግራችሁ፣
ከእንግዲህ አይመጣም ፈታኝ በቤታችሁ።
ወደፊት ነው እንጂ ሥርዓት አስከብሮ፣
ወደ ኋላ ማለት እሱ ቀረ ዱሮ።
የነገ ካህናት ሕዝብን የምትመሩ፣
በሰላም በፍቅር በሃይማኖት ኑሩ።

ከትሕትና ጋር መልካም ነገር አይቷል፣
በዲያቆን መኮንን ሁሉም ተደስቷል።



# ዲያቆን መኮንን

በሁሉ ሙሉ ነው እጅጉን አስተዋይ፣
ጥበብ ማስተዋልን አምላክ ሰጥቶት ከላይ።



# ዲያቆን ኤርምያስ

መልካም ነገር ማድረግ ከአንተ ለተሰጠው፣
ለዲያቆን ኤርምያስ በረከት አድለው።
መታዘዝን ያውቃል አጽናለት እምነቱን፣
አብዝተህ አድለው ማስተዋል ጥበቡን።

በምን ይገለፃል እንደ ሰው ሲታሰብ፣
ቤዛ-ኩሉ ማለት የሁሉ ቤተሰብ።



ግንቦት ፴/፳፻፯ ዓ.ም.

# ቤዛ-ኩሉ ሰንበት ት/ቤት

በፍቅር የኖራችሁ የሃይማኖት ሰዎች፣
ወጀብ አልፋችኋል የክርስቶስ ልጆች።



አቶ አበጀ፤ ወ/ሮ ፍቅርተ፤ አቶ ተካልኝ፤ አቶ ለዓለም፤ አቶ ደምስ፣ ወ/ሮ ገነት፤ ወ/ሮ
አቶ ይመር፤ ወ/ሮ ካሰች፤

በሰዎች ላይ አድሮ እግዚአብሔር መርጧችሁ
ሕዝቡን በማገልገል ቤቱን የመራችሁ፣



አቶ መኳንንት።

በእውቀት በገንዘብ በጊዜ በጉልበት፣
ብዙ ደክማችኋል እናውቃለን በእውነት።
ስለሠራችሁት ድንቅ መልካም ነገር፣
እንዲህ እንመስክር እንዲህ እንናገር።
ከኃላፊነት ጋር እንቅልፍ እያጣችሁ፣
ሕዝቡን በአርአያነት አስተዳደራችሁ፣
ከእኛ አንደበት ይውጣ እንመርቃችሁ፣
የሰሎሞን ጥበብ ይደር በላያችሁ።
ከኃጢአት በስተቀር ይድረስ የልባችሁ፣
እናንተንም ደግሞ እግዚአብሔር ይምራችሁ።

ሁላችንም ዛሬ አንድ ነገር ቀረን፣
ሊፈጸም የሚችል እንዲህ ሕብረት ካለን።
ቋንቋችን ግልጽ ነው ያለው ከእኛ አንደበት፣
ለእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ማዘጋጀት።
ቤት ሥሩልኝ ብሎ አምላክ የመረጠን፣
እንዴት ቢወደን ነው ለዚህ ክብር ያሰበን።
በእግዚአብሔር ይወደድ የእውነት ግብራችን፣
የሥላሴ ክብር ይግባ በቤታችን።



ሕፃናት በመዝሙር አገልግሎት።

በኩልትፍ አንደበት የአምላክን ስም ጠርተው፣
ምስጋና እንዲያቀርቡ አንደበት አውጥተው፣
የጊዜ መሥዋዕት እጅጉን ከፍላችሁ፣
ከሕፃናቱ ጋር ወጥታችሁ ወርዳችሁ፣
“ሀ ለ ሐ መ” እያሉ ፊደል እንዲቆጥሩ፣
ሃይማኖታቸውን ከአሁኑ እንዲማሩ፣
ከቅዱስ መጽሐፍ ቃል አስተምራችሁ፣
እግዚአብሔርን ፈሪ እንዲሆኑ አርጋችሁ፣
ከባድ ኃላፊነት ለተወጣችሁት፣
ሕፃናቱን ምግባር ላስተማራችሁት፣
ለእናንተ የሚስማማ ምን ዓይነት ቃል ይውጣ፣
ከምድር አይገኝም ከሰማይ ካልመጣ።

ልዑል እግዚአብሔር
ወባርክን ያባርካችሁ!!!

አንዲት ክፍል ውስጥ ሠላሳ እና አርባ ሰው፣
እንዲወጡ ማስቻል ተዋደው ተፋቅረው፣
ከእግዚአብሔር ነው እንጂ መቼ ከሰው ይባል፣
የሥራችሁ ፍሬ ፅፁብ ነው ያስብላል።

የሚስተዋል ሥራ ድንቅ ያደረጋችሁ፣
ከማያልቀው ፀጋ እግዚአብሔር ይስጣችሁ።
ቃላት አይገልጸውም ግሩም ነው ሥራችሁ፣
አሁንም አብዝቶ አምላክ ይባርካችሁ።

እናንተም ሕፃናት መሥሪያ ቤት ሠርታችሁ፣
ገንዘብ ባታገኙም ባይከፈላችሁ፣
ከአባት ጠይቃችሁ ከእናት ለምናችሁ፣
ብር ሰጥታችኋል ለእግዚአብሔር ብላችሁ።



**ሕፃናት በመዝሙር አገልግሎት።**

ወላጅ ጊዜ አግኝቶ የሚያገለግለው፣
ግማሹን ተሻምቶ ከእናንተ ወስዶ ነው።
መቼ በገንዘብ ብቻ ርዳታ ረዳችሁ፣
በጌታ ፊት ቀርቧል ጊዜም አዋጥታችሁ።



እናንተ ሕፃናት ስለ እናንተ ብሎ፣
እግዚአብሔር ይርዳን ቤት ይስጠን በቶሎ።
ስለ ሃይማኖት ክብር ቃላችን አይነጥፍም፣
እናንተን ማስተማር በጭራሽ አንሰንፍም።
ፍቅር የምታውቁ የፍቅር ሰው ናችሁ፣
ጣዕመ እግዚአብሔርን ይወዳል ልባችሁ።

እኛም ካህናቱም ዲያቆናቱም ሆነን፣
የእውነት መንገድን እናስተምራለን።
እንዳሰብነው ይሁን እንመርቃችሁ፣
እግዚአብሔር እምነትን ይጻፍ በልባችሁ።
እንደ እኛ ባይሆንም ባይወጣም ድምጻችሁ፣
እጅግ ትልቅ ነገር ያስባል ውስጣችሁ።
በሃይማኖት ኑሩ ሃይማኖት ይዛችሁ፣
ለእምነት ተቆርቋሪ አምላክ ያድርጋችሁ።



አንቺ እናት ጸሎትሽ እንባሽ ገሰገሰ፣
የራሔል ለቅሶ ነው ፀባዖት ደረሰ።
መቼ ሰንካላ ነው ከእንግዲህ አምልኮሽ፣
የድንግል ልጅ ጌታ ክርስቶስ አክብሮሽ።
ማዕበሉን ተሻገርሽ ልጆችሽን ይዘሽ፣
በፍሥሐ ኑሪ በሃይማኖት ፀንተሽ።

ድንግልን ይዘናል ኪዳነ ምሕረትን፣
ከእንግዲህ አናፍርም አግኝተን ፅናትን።
እስከ ዘላለሙ ተናግረን አንፈር፣
ቅዱስ አምላካችን መድኃኔዓለም ክበር።/፪/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

አብርሃም ሰሎሞን።
Abraham Solomon
slat6@yahoo.com
ግንቦት ፴/፳፻፲ ዓ.ም.